

# በረመዳን ደም እምባ!



የጐንቻው!

በቅዱስ ረመዳን ለነብዬ በመስጊዴ ተወስኘ፤
በጾም፤በጸሎት በተጋሁ ሰላም ፍቅርን ተማጥኘ፤
ጾብ በሸሸሁ ለአገር ለወገን ለሁላችን ወግኘ፤
ስዋከብ የኖርኩ በጅምላ በካሃዲዎች ተመዝኘ፤
ስሜን ጥላሸት ቀብቶ 'ሽብርተኛ' እንድሳደድ ታድኘ፤
አካል ጉልበቴን ለመንፈስ ምልጃ ምግብ ቀንኘ፤
ሰላም፤ ፍቅር፤ እርቅ፤ ነጻነት እየሰበኩሁ ተማጥኘ፤
ዓመት ተመንፈቅ ሰማይ ምድሩን ቅን ለምኘ፤
**ወያኔማ! እልህ፤ አሳር፤ ሽብር ግድያ ነው የተቃኘ።**

ሃይማኖቴን፤ የእምነት ቤቴን ረጋግጦ ያረከሰ፤
ትልቅ ስሜን፤ ሃገር ክብሬን አወራርዶ ያኮሰሰ፤
ጦር አዝምቶ፤ ታንክ ነድቶ፤ አነጣጥሮ የተኮሰ፤
የንጹሃንን ሕይዎት በቅልብ አጋዚ ያስጨረሰ፤
በጎዳናው፤ በአድባባው፤ የግፍ እንባ ያሳፈሰ፤
ምዕመናንን፤ኢማም፤ አስሮ፤ ሕገ ደንቡን እየጣሰ፤
አኬልዳማ፤ጃሃዳዊ ሃርካት ሽብር ድራማ እየቀየሰ፤
**እነሆ! በአሳሳ፤ሻሸመኔ፤በኮፈሌ ደም አበላ ያፈሰሰ፡፡**

ከእንግዲህስ! በቃህ በለኝ፤ ስንቴስ ልሙት በቁሜ፤
አንተ አምላኬ፤ ነብዬ! የምማጸንህ በእውኔና በህልሜ፤
ፍርዱን ስጠኝ በምድር ከንቱ ፈሶ አይቅር እምባ ደሜ፤
የገዳዬን ጡንቻ አስልለህ ጉልበት ሁነኝ መከታ እድሜ፤
ዛሬ ይሁን፤የዘረኛው፤የግፈኛው፤የወያኔው ሥርዓተ-ፍጻሜ፤
**እንድዘክር 'ረመዳን ሰደቃ' በእስላም ክርስትያኑ በወገኔ ታድሜ፡፡**

*በግፈኛውና ዘረኛው ወያኔ በቅርቡ በኮፈሌ፤በአሳሳ፤በሻሸመኔ ለተገደሉ ወንድምና እህቶቻችን መታሰቢያና ለወላጅ ቤተሰቦቻቸውም መጽናኛ ትሁንልኝ።*

የጐንቻው! 04.08.13
yegonchaw@yahoo.co.uk